Embassy of the
Kingdom of the Netherlands

# የጋራ ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
*2015/29*

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

---

## አሜሪካና ኔዘርላንድ የኢትዮጵያን የወተት ሀብት ዘርፍ ለማጠናከር በጋራ እየሠሩ ነው

### *የተደረገው ስምምነት በኢትዮጵያ በወተት ልማት ዘርፍ የተሰማሩ በሺ የሚቆጠሩ የባለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮችን ገቢ ያሳድጋል*

**አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፤ነሐሴ 28 ቀን 2007 ዓ.ም.፡-** የአሜሪካ መንግሥት በአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲው በኩል አዲስ አበባ ከሚገኘው የኔዘርላንድ ኤምባሲ ጋር በመተባበር የኢትዮጵያን የወተት ዘርፍ በማሳደግ ዙሪያ በጋራ ለመሥራት ስምምነት ተፈራረመ፡፡ ትብብሩ ከሁለቱም ወገኖች በሚገኝ ሙያዊ ድጋፍ በዘርፉ ያሉ አቅራቢዎችን፣አርሶ አደሮችን፣አቀነባባሪዎችን፣ሸማቾችንና ላኪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡

የአሜሪካና የኔዘርላድ መንግሥታት፤ የኢትዮጵያ የወተት ልማት ዘርፍን በመደገፍ ረገድ ላለፉት አሥር ዓመታት ግንባር ቀደም ሚና ሲጫወቱ ቆይተዋል፡፡

በኢትዮጵያ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር ባደረጉት ንግግር፡-“ባለፉት ዓመታት ባደረግናቸው ጥረቶች፣ ዘርፉን ከነበረበት የጨቅላነት ደረጃ ለኢትዮጵያ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ሊሆን ወደሚችል ኢንዱስትሪ ልናሸጋግረው ችለናል፡፡ ይህ በአሜሪካና በኔዘርላንድ መንግሥታት መካከል የተፈጠረው አጋርነት፣ ሁለቱ ሀገራት በኢትዮጵያ በወተት ሀብት ልማት የሚሰጡትን ድጋፍ ከፍ በማድረግ ረገድ እንደ ታሪካዊ እርምጃ የሚወሰድ ነው” ብለዋል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ የእንስሳት ገበያ ልማት መርሀ ግብርና የኔዘርላንድ ኤምባሲ የወተት ንግድ መረጃና ድጋፍ አገልግሎት ፕሮጀክት ተገቢውን ሙያና ልምድ ለዘርፉ ዕድገት ያበረክታሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ስምምነቱ ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት የሚዘልቅ ሲሆን፤የኢትዮጵያን የወተት ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ ያሻሽላል ተብሎም ይታመናል፡፡

በሺህ ከሚቆጠሩ ባለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች ምርት የሚረከቡ የወተትና የወተት ተዋጽኦ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎችን ለመደገፍ የሚደረገው የተቀናጀ ጥረት፤ በዘርፉ ለተሰማሩት የገበያ ዕድል ከመፍጠሩም በላይ፤ ምርት አቅራቢ አርሶ አደሮች ተረካቢዎች የሚፈልጉትን የጥራት ደረጃ ለማሟላት በይበልጥ ይተጉ ዘንድ ያበረታታል፡፡ ይህም በበኩሉ የሸማቹ ማህበረሰብ ደህንነት የተጠበቀ እንዲሆን የሚያደርግ ይሆናል፡፡

የኔዘርላንድ ኤምባሲ ምክትል አምባሳደርና በኤምባሲው የልማት ትብብር ኃላፊ የሆኑት ሚስተር ማርቲን ኮፐር በበኩላቸው፡-“ይህንን የመግባቢያ ሰነድ በመፈረማቸው፤ የአሜሪካና የኔዘርላንድ መንግሥታት ወሳኝና ውስብስብ በሆነው የወተት ልማት ዘርፍ በተናጠል ከሚያርጓቸው ጥረቶች ባሻገር

ፍሬያማ የሆነ መደበኛ ትብብር እንዲመሠርቱ አስችሏቸዋል። ይህም በየግላችን በምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ላይ እሴት ጨምሮ በምርት ሂደቱ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ይሆናል። በሌላም በኩል ለጋሽ መንግሥታት ተቀናጅተው ከሠሩ፤ በሚሰጡት የልማት ድጋፍ የበለጠ ስኬታማ ይሆናሉ የሚል መልዕክት ለመላው ዓለም እናስተላልፋለን" ብለዋል።

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ የእንስሳት ገበያ ልማት የአሜሪካ መንግሥት መጪውን ትውልድ መመገብ የተሰኘ መርሀ ግብር አካል የሆነ የአምስት ዓመት ፕሮጀክት ሲሆን፤ዓላማው ባለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮችን ገቢ ማሳደግና የአራት ክልሎች ነዋሪዎችን የሥርዓተ ምግብ ሁኔታን በማሻሻል ላይ ያተኮረ ነው።

የወተት ንግድ መረጃና ድጋፍ አገልግሎት በኔዘርላንድ መንግሥት ድጋፍ የሚደረግለት የሦስት ዓመት ፕሮጀክት ነው። የፕሮጀክቱ ዓላማ በኢትዮጵያ የግሉ ዘርፍ በወተት ምርት ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችና ድርጅቶችን ግንኙነት በማሻሻል፣ጥራት ያለውና ጠቃሚ የሆነ የንግድ መረጃ መኖሩን በማረጋገጥና የምክር አገልግሎት በመስጠት ዙሪያ ድጋፍ የሚሰጥ ነው።

###

###